# ሕልሞችና ፍቺዎቻቸው

Dreams and Interpretations

*[ኢዩኤል 2:28](#)፤ ከዚህም በኋላ እንዲህ ይሆናል፤ መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈስሳለሁ፤ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ፥ ሽማግሌዎቻችሁም ሕልምን ያልማሉ፥ ጐበዞቻችሁም ራእይ ያያሉ።*

የተወሰኑት ህልሞቼ ስብስብ ከተቀበልኳቸው ትርጓሜዎቻቸው ጋር።

እንደአጋጣሚ ሆኖ፥ከ20ዎቹ ውስጥ የአንዱን ብቻ ነው ግልጽ የሆነ መረዳት ያገኘሁት።

---

## **መነጠቁ** (ሜይ 07)

(Rapture : May 07)

በጣም ግልጽ ግን ወሳኝ (profound) መልዕክት፥ከመነጠቁ በኋላ የቀረ (left behind) ሰው እያየሁ ነበር። ጠንካራ፥ የሚስብ፥ የክህነት ልብስ የለበሰ ሰው ነበር። በውስጡ ግን ሰይጣን ነበር። እንዲህ አለ፥ *“ምናልባት የተሰወሰኑ ተጨማሪ የድግምት (incantation) ቃላትን ብናገር እወሰድ ይሆናል።”*

ለምን እንደቀረ ግራ ተጋብቶ ነበር። ወዲያውም በተሳሳተ መንገድ በመመራቱና የመነጠቁ አካል ባለመሆኑ ምክንያት የተቆጣ ከተከታዮቹ አንዱ መጣ። የካህኑ የቀድሞ ተከታዮች ሊገድሉት መጡና በመጨረሻም ካህኑን አድነው ያዙት።

**ከእግዚአብሔር** ባልሆኑ ካህናት ላይ የሚደርሰውን የሚያሳይ ግልጽ መልእክት።

---

## **ቆሻሻ በግ** (ማርች 2፥07)

በምሽት የተከማቹ በጎችን እያየሁ ነበር። ሁሉም ያደፈና ቆሻሻ ጸጉር ነበራቸው፥ እንዲሁም እርስ በእርሳቸው ተጠጋግተዋል፥የሆነ ነገር የፈሩ ዓይነት። እርስ በእርስ ቢጠጋጉ የሚጠበቁ ሆኖ ተሰምቷቸዋል። ስህተት! 10 ጫማ (3 ሜትር) ሰይጣን የመሰለ ኮርማ (Bull)፥ ግዙፍ ቀንዶች ያሉት፥ በኋላ እግሮቹ እየተራመደ፥ ወደ መንጋው መጣ፥ አንዱንም ከመሀል ወስዶ ገነጣጠለው። ምንም ጥበቃ አልነበራቸውም። ይህ ከተፈጸመ በኋላ፥ ወደ እኔ ተመለከተኝና ተናገረ። ስለምን እያወራ እንደነበር አላስታውስም፥በጊዜው ተደብቄ ነበር።

ከነቃሁ በኋላ ይህ ሰይጣን ኮርማ በበጎቹ ላይ ኃይል (ስልጣን) የነበረው ቆሻሻ ስለነበሩ እንደሆነ ማጠቃለያ ላይ ደረስሁ። እናም ኢየሱስ እንዳስጠነቀቀው ዓይነት እንደነዚያ የማይጠቅሙ የበግ እረኞች እንዳልሆን ጸለይሁ፥ልክ በመጀመሪያው የመከራ ምልክት ጊዜ እንደሚሮጡት (እንደሚሸሹት)!

---

## **ለሚመጡት ነገሮች ተዘጋጁ** (ዲሴምበር 06)

የጋራ አላማ ያላቸው ብዙ ህልሞችን አይቻለሁ፥ ለበለጠና ለበለጠ ማእበሎች፥ መብረቅና ነጎድጓድ የቀላቀለ አውሎ ንፋስ(storm) ና ፈተናዎች ተዘጋጁ። በሰማይ 10 ማይል (16093 ሜትር) የሚያህሉ፥ ብርቱና ዝግጁ ያልሆነውን ማንኛውንም ነገር ጠርገው መውሰድ የሚችሉ፥ መብረቅና ነጎድጓድ የቀላቀሉ ግዙፍ አውሎንፋሶችን አይቻለሁ። ባየሁት በአንዱ ህልም ውስጥ፥ በቅርቡ በመንፈስ የተሞሉትና የተዘጋጁት ብቻ በሚመጡጥ ቀናት መቆም እንደሚቻላቸው አይቻለሁ፥ መብረቅና ነጎድጓድ ከቀላቀለው ከታላቁ አውሎንፋስ የተነሳ ባለስልጣናትና ጥሩ ሰዎች እንኳን ይወድቃሉ።

በዚህ ወር ያየኋቸው ህልሞች በመጠኑ ግልጽ ነበሩ፥ የጨለማው ስልጣናት እያደጉ ይሄዳሉ፥ ከመቼውም ጊዜ የበለጠ አስፈሪና ኃያል ሆነው። በአንድ ህልም በሰይጣን የተፈበረከ ማሽን አየሁ፥ ብዙ ሰዎች ቅባቱን ለማግኘት ቆመዋል። አንድ ሰው በውስጡ ሲያልፍ፥ የበለጠ ጠንካራ ሆኖ ይወጣል፥ በአውሬ (beast) ዓይነት ብርታት፥ እንዲሁም ጭራቅ (አውሬ)(monster) በሚመስል አቋም። ሰይጣኑ ይህን ኃይል በተቻለ መጠን ለብዙ ሰዎች ለመስጠት ይሞክራል፥ እናም በ(ማሽኑ) ውስጥ ያላለፉት ሰዎች ከእነዚህ አዲስ ከተዳቀሉት ሰዎች አንጻር ሲታዩ ‘ልፍስፍስ’ መስለው ቆመዋል።

(ዳንኤል 2:43፣ *ብረቱም ከሸክላው ጋር ተደባልቆ እንዳየህ፥ እንዲሁ ከሰው ዘር ጋር ይደባለቃሉ፤ ነገር ግን ብረት ከሸክላ ጋር እንደማይጣበቅ፥ እንዲሁ እርስ በርሳቸው አይጣበቁም።*)

---

**የጌታን ኃይል ያለአግባብ መጠቀም** (ዲሴምበር 31፥05)

የተረገምሁ ሰው ነኝ፥ እራሴን ጌታ ኃይል ሰጥቶኝ ያለባቸው ብዙ ህልሞች ውስጥ አይቼዋለሁ። እናም ይህ ኃይል አበላሽኝ (corrupts me)፥ ሁል ጊዜም ያለ አግባብ የምጠቀምበት ይመስላል። ሰዎችን ከጌታ ይልቅ ወደ ራሴ ለማምጣት እየተጠቀምሁበት። በራሴ በጣም ተስፋ ቆርጬ ተነሣሁ፥ ሌላ ፈተና ወደቅሁ። ጌታ የሰዎችን ልብ ይመረምራል፥ እናም ጥልቅ ወደውስጥ ያለው የተወሰነው እኔነቴ የተበላሸ ይመስላል። የጌታ ኃይል እርሱን ለማገልገል ብቻ ነው፥ ለእኛ ክብር እንዲሰጡን አይደለም!

---

**ጓደኞቻችሁን መሰብሰብ** (ኦክቶበር 16፥05)

በዚህ ህልም ወስጥ እራሴን ከብዙ የአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ጓደኞቼ ጋር አየሁ፥ ከተረሱ የቆዩ ሰዎች። ምንም እንኳን ሰውነታችን በአንድ አካላዊ ቦታ ቢወሰንም፥ መንፈሳችን ግን በዚህ መልኩ እንዳልተወሰነ መረዳቱ ተሰጠኝ። እናም ካለፈው ህይወት ሁሉንም ጓደኞቻችንን ወደ መንግሥቱ መሰብሰብ እንዳለብን። በጸሎት፥ በምልጃና ለእነርሱ በመጓዝ፥ ምንም እንኳን በየቀኑ ባናያቸውም።

---

የማርች 21፥05 ሕልም

“*በቤተክርስቲያን ያሉ ይሁዳዎች*”

በዚህ ማለዳ ያየሁት ሕልም አስፈሪ ነበር። የጦር አውሮፕላን ካምፕ (base) አየሁ፥ የጌታን ቤተክርስቲያን ወክሎ። መሣሪያ የታጠቁ እግረኛ ወታደሮች፥ አውሮፕላኖች፥ ተዋጊ ፓይለቶች፥ ጠባቂዎች፥ የጦር መሪዎች ወዘተ ነበሩ። ሁሉም ነገር መልካምና በአግባብ ይመስል ነበር፥ ከዚያም የሆነ ሁኔታ አስተዋልሁ። እያንዳንዱ በየራሱ ግዳጅ እየተሰማራ ነበር በድንገት፥ ብዙ የእግረኛ ኃይላችን ቡድን (ስቶርም ትሩፐርስ የሚመስሉ) በፍጹም አንድነት ወደ አንድ ክልል መሄድ ጀመሩ። ከአውሮፕላኖቹ ማቆሚያ (ኤርፕሌን ሀንገር) በጣም ከፍ

ብሎ ወዳለ ወደዚህ ወደ አንድ የእንጨት መድረክ ሲሄዱ (marching) አየሁ። በወታደራዊ የሰልፍ እርምጃ ነበር የሚሄዱት፥ እናም በአንድ በማይታይ ኃይል ትእዛዝ ይሰጣቸው ነበር። በዚህ መድረክ መሳይ ጠርዝ ሲደርሱ ሁሉም መሣሪያቸውን አወጡ። (AK-47s፤ ኤኬ-47ኦች) በአድናቆት ተመለከትሁና ለራሴ "*እናንተ ሰዎች ምን እያደረጋቹ ነው? ለማን ነው እየመለሳችሁ ያለችሁት?*" አልኩኝ። የመጀመሪያው አውሮፕላን ከማቆሚያው ሲመጣ፥ ወታደሮቹ ሁሉ ተኮሱበት። ለአብራሪው ምንም እድል አልነበረውም፥ አውሮፕላኑን የሚያወድም የጥይት እሩምታ ወረደበት። አብራሪው ከጥይቶቹ ለማምለጥ በሚያበቃ ፍጥነት መሄድ አልቻለም። አንድ ቃል ወደ አእምሮዬ ዘለለ "**ክህደት**"። የዚህ ቡድን አባል ያልሆነ ወታደር ሁሉ በፍርሀት መሮጥ ጀመረ። አብራሪዎቹ ሁሉ ከዚህ ማቆሚያ በከፍተኛ ፍጥነት ለመሄድ ሞከሩ፥ ነገር ግን ምንም እድል አልነበራቸውም። ጎበዝ ተዋጊ አብራሪዎቻችን ሁሉ እያጣን ነበር። ከዚያም አንዱ አብራሪ ሌላ መስመር ተጠቀመ። ለማምለጥ በመሞከር ፈንታ፥ አውሮፕላኑን መድረኩን ወዳቆሙት ምሰሶዎች አዞረ፥ እናም በውስጡ ተከሰከሰ፥ ራሱን በመሰዋት። ይህ ሰዎቹን የያዘውን መሠረት አፈረሰው፥ እናም ከከሀዲዎቹ ወታደሮች ብዙዎቹን ገደለ። ይህ ከተከሰተ በኋላ፥ በሆነ ሁኔታ፥ የጠሩን አንድነት ሰበረው፥ ወደ ድብልቅልቅ ሁኔታ ውስጥ ከተታቸው። እንደዛም ሆኖ ለእኛ አደጋ ነበሩ፥ ነገር ግን ከዚህ በኋላ በጋራ እየሠሩ አልነበሩም። ከታማኝ ወታደሮቻችን አንዱ ሬድዮውን አንስቶ "*የሹዋን (ኢየሱስን) እንፈልጋለን!*" አለ። ህልሙ አበቃ።

---

**ጸጋ መካፈል** (ዲሴምበር 31፥04)

በሕልሙ ውስጥ፥ አንዳንድ ክርስቲያኖች በሰዎች ላይ እጃቸውን ሲጭኑ፥ በክርስቲያኖቹ ውስጥ **እግዚአብሔር** ያስቀመጣቸው ልዩ ነገሮች ወደ ተነኩት ሰዎች ሲተላለፉ አየሁ። እጆቼን በሌላ ሰው ላይ አየሁ፥ እናም ከዚያ ሰው ላይ የሚዘሉ የሆኑ ቃላት በእጄ ላይ ነበር።

**ራስን መግዛት፥ ፍርድ፥ እግዚአብሔርን መፍራት፥ ብስለት**። (ሌሎች ክርስቲያኖች ሊያካፍሏቸው የሚችሏቸው ሌሎች ጸጋዎች ነበሯቸው።)

ይህ በጣም አስፈላጊ ስጦታ ነበር፥ በሚታወቅ ሁኔታ የብስለቱን ሂደት እያፋጠኑ። እንደዚህ ዓይነቱ አገልግሎት "**እጅን የመጫን**" ችላ ሊባል አይገባም።

---

**ጎማ የሆኑ ተናጋሪዎች** (ዲሴምበር 24፥04)

ብዙ ጊዜ አንድ ሰው ስለየሆነ ርዕስ ሲያስቸግረኝ ሰላሜን አጣለሁ። ወደ ጭቅጭቅ ወይም ጠብ ውስጥ እንዳልገባ ራሴን ከእነርሱ እለያለሁ። ካልተከራከርሁ በመንፈስ ለመቆየት ቀላል ሆኖ አግኝቼዋለሁ። በህልሜ፥ ከዲጄው አለቃዬ ጋር ምን ዓይነት የሙዚቃ ስፒከሮችን እንደምፈልግ እየተወያየሁ ነበር። መቋቋም የሚችል በጎማ የተሸፈነ ትንሽ ስፒከር ነበረኝ። ነገር ግን እንደትልልቆቹ በእንጨት እንደተሸፈኑት ስፒከሮች ኃይል አልነበረውም፥ ነገር ግን ምትን መቋቋም የሚችልና በመጠኑም ቢሆን ጮኽ ብሎ ይሰማል። ከደረጃ ላይ እንኳን ብትወረውሩት ተመልሶ ይሠራል። በህልሜ ውስጥ ለአለቃዬ በጎማ የተሸፈነው ዘላቂው ስፒከር በቀላሉ ከሚሰበረው ከኃይለኛው ስፒከር እንደሚሻል እያሳመንኩት ነበር። ጉዳዬን ካቀረብሁ በኋላ ወዲያው፥ ግብዝ እየሆንኩኝ እንደሆነ ባለ ስሜት ውስጥ ሆኜ ነቃሁ። በአንድ በኩል በመንፈስ ለመመላለስ ተቃዋሚዎችን መሸሽን እመርጣለሁ፥ (ያም በቀላሉ የሚሰበረውን የእንጨቱን ስፒከር ይወክላል) በሌላ በኩል ደግሞ ሙዚቃ ወደማጫወት ሲመጣ፥ መቋቋም የሚችለውን የጎማውን ስፒከር እመርጣለሁ (ይህም ማለት የአንዳንድ ስብእናዎችን ስንጥቅና ቡጭሪያ ይወክላል።)

---

## የኖቬምበር 23÷03 ህልም

*በውኃ ዳርቻ ጠርዝ ላይ ነበርሁ እና ሞገዱ ከፍ እያለ ከፍ እያለ ይመጣ ነበር÷ በጣም በቅርቡ ወደላይ ወደዳገቱ ለመውጣት አልያም ተመቶ ለመውደቅ እገደዳለሁ። ማእበሉ የሰዎችን ቤቶች እየወሰደ ነበር÷ ነገር ግን ወደ ውጭ እየሮጡ አልነበረም። አንዳንዶቻችን ውኃው ከፍታውን ሲጨመር ድምጹ ከሩቅ ይሰማን ነበር÷ እናም ሌላ የበለጠ እንደሚመጣ መናገር እንችል ነበር። ሙሉ የማእበል ክምችት ከመጣ በኋላ÷ በየቦታ የመፈራረስ ሁካታ÷ ነገሮች በጥቂቱ ተረጋጉ።*

*የእኔ ፍቺ፡*

*በውኃ ዳርቻዎች የሚወሰዱ ሰዎች ይኖራሉ÷ ለህይወት እያጣጣሩ። እንዲሁም ንብረቶች በውኃ ዳረቻዎች ይወሰዳሉ። ስለዚህም ልረዳቸው ወደዚያ ወረድሁ÷ ነገር ግን ከተለያዩ ክፍሎች ተቃውሞ ገጠመኝ። ማእበሉ መንፈሳዊ ጨለማ እንደሚወክል መረዳት ተሰጠኝ። እናም በምድር ላይ እየጨመረ ነበር። አለመታደል ሆኖ ብዙ ሰዎች በእነርሱ ታጥበው ተወስደዋል። ከውኃ ስር መሆናቸውን እንኳን አላወቁትም ነበር። እናም ወደ ዳገቱ ለመውጣት ፈቃደኛ አልነበሩም። እነዚህ ሰዎች በአካላቸው÷ በማህበራዊ ህይወታቸው÷ እንዲሁም በገንዘብ ጥሩ ሊሆኑ ይችላሉ÷ ነገር ግን በመንፈስ እየሰመጡ ነበር። እምነታቸው÷ ምንአልባትም በአንድ ወቅት ይንቀሳቀስና ያድግ የነበረ÷ አሁን እየሞተ ነበር። ምን አልባት ወደ ቤተክርስቲያን መሄዳቸውንና መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት ሊቀጥሉ ይችላሉ÷ ነገር ግን ለአ**ዳኛቸው** ካለ ፍቅር የተነሣ ከሆነው ይልቅ እንደ ልማድና ግዴታ ነው። ሙሉ በሙሉ መውደቃቸው የጊዜ ጉዳይ ነው። ምክንያቱም ምንም አየር እያገኙ አልነበረም።*

*በውኃው ዳር ከተወሰዱት መሀከል **አዳኙን** የሚፈልጉም ነበሩበት÷ ነገር ግን ለጠላት ድንገተኛ ጥቃት ዝግጁ አልነበሩም። ያለባችሁን ኃጢአት አስታውሱ ትንሿ እንኳን በመንፈሳዊ ውጊያ ውስጥ ግዙፍ ሸክም ትሆናለች። እናም ማእበሉ እነዚህን ጉዳዮች ወደ ግልጽ አመጣቸው። ስለዚህም እኛ በማእበሉ የጸናን (የበረታን) እነዚህን የተረፉትን ልንታደጋቸውና ሀብቶቹን የመሰብሰብ ሀላፊነት አለብን÷ ነገር ግን ይህን ስናደርግ ለታላቅ ተቃውሞ (ተግዳሮቶች) ዝግጁ ልንሆን ያስፈልገናል።*

---

## የኖቬምበር 27÷03 ህልም

*በዚህ ህልም ውስጥ÷ **ኢየሱስ** ተመለሰ÷ እናም ከሁሉም አገልጋዮቹ ጋር መነጋገር ጀመረ። ሁላችንም በመመለሱ ተደንቀን ነበር÷ እናም ለሁላችንም ከኃይሉ ከፍሎ ሰጠን። እነዚህን የሰጠኝን አንዳንድ ስጦታዎች (ጸጋዎች) ለመሞከር ወጣሁ÷ እናም ታላቅ የሆነን ጋኔል መዋጋት ጀመርሁ÷ ከእኔ ሰውነት 10 እጥፍ የሚበልጥ። **ኢየሱስ** በሰጠኝ በአዲሱ ኃይል÷ ይህን ጠላት ማሸነፍ በጣም ቀላል ነበር። ይህ ታላቅ ደስታን ሰጠኝ÷ ነገር ግን የሆነ ክፉ ነገር እየሆነ እንዳለ አስተዋልሁ። የ**ኢየሱስ** ኃይል ሊያበላሸን ሲጀምር* (begun to corrupt us) *አየሁ÷ ሥጋዊ የሆንነውን። ወዲያው አንዳንድ አገልጋዮቹ አንዱ በአንዱ ጸጋ (ስጦታ) ሲቀና አየሁ። እናም እርስ በእርሳችን መከራከር ጀመርን÷ እንዲሁም በስፍራችንና በደረጃችን ስንሟገት። አንዳንዶቻችን ለዚህ ኃይል የበሰልን መሆን አለመሆናችን ግልጽ ሆነ። (**በእግዚአብሔር** ኃይል ቅባት ስባረክ÷ ለማሳየት በጣም ጉጉ ነኝ÷ ልጎርርበት÷ በትንሿ መነሳሳቴ ልጠቀምበት በጣም ጉጉ ነኝ።)*

---

## የፌብሯሪ 1÷04 ህልም

በዚህ ህልም ውስጥ፥ ከሌሎች ሰዎች ጋር በባሕር ላይ እየተንሳፈፍሁ ነበር፥ ትልቅ “ታይታኒክ”ን ከሚያክል መርከብ ፊትለፊት። ከዚያም የመርከቡ የፊቱ ጫፍ ሳይታወቅ ተገነጠለ፥ እናም መርከቡ ውኃ ማስገባት ጀመረ። በውኃ ውስጥ የነበርን አንዳችንም በዚህ ነገር ንቁ አልነበርንም፥ መርከቡ ትልቅ ስለነበር፥ አሳሳቢ አይመስልም ነበር። አንድ (ምልክት ማሳያ) ርችት (ፍሌር flair) ይገዬ ነበር፥ ነገር ግን መጠቀሙ አስፈላጊ አይመስልም ነበር። ለተወሰነ ጊዜ ውኃ ከገባባት በኋላ፥በውኃ ውስጥ ያለነው “*ያ መርከብ የፈለገ ትልቅ ቢሆን አይገደኝም፥ ይሰምጣል*” ማለት ጀመርን። ችግሩ ማንም ዘሎ የሚወርድ አለመኖሩ ነው። እናም ሲሰምጥ፥ በፍጥነት ወደ ታች ወረደ። ወደ ጥልቁ ተከትዬው ዋኘሁ እናም ግን ልደርስበት አልቻልሁም።

ከጸሎት በኋላ፥ መርከቡ ኢኮኖሚን እንደሚወክል መረዳትን አገኘሁ። የራሴን የኢኮኖሚ ሁኔታ ማስተካከል እንዳለብኝ እየጠቆመኝ፥ እንዲሁም ወጪዬን በጣም እንዳልለጥጥ። የአብዛኛዎቹ ህልሞቼ ተደጋጋሚ መልእክቶች ነበሩ። ሁላችንም *ሥራችንን* (our roots) መትከል እንዳለብን፥ እምነታችንን ማጠንከር፥ እንዲሁም ለሚመጣው ለማንኛውም ነገር ዝግጁ መሆን።

ለእኔ ብቻ እንጂ ለሌላ ሰው ትርጉም የማይሰጡ ብዙ ህልሞች አይቻለው፥እኔንና እኔ የማውቃቸውን ሰዎችና ቦታዎች የሚመለከቱ። ነገር ግን አንድ ያየሁት የድርጊት ሂደት (pattern) አለ። ልጸልይላቸው ስለሚገቡኝ ሰዎች፥ ላስተካክላቸው ስለሚገባኝ ጉዳዮች(ችግሮች)፥ ልናዘዛቸው ስለሚገቡኝ ኃጢአቶች ህልሞችን አይቻለሁ። ነገር ግን ከእነዚህ ህልሞች ቀጥሎ ወዲያው፥ የ”*ኃጢአት ህልም*” አያለሁ፥ ከባድ ፈተና ይሰጠኝ ነበር። በዚህ ፈተና ብወድቅ፥ (*ብዙ ጊዜ እንዳደረግሁት*) የመጀመሪያውን ህልም ረሳዋለሁ፥እናም መተኛቴን እቀጥላለሁ። ነገር ግን ፈተናውን ከተቋቋምሁት፥ እነቃለሁ፥ የመጀመሪያውን ህልም አስታውሰዋለሁ፥ እናም ለማማለድ ብርታትን አገኛለሁ።

---

## የቅርብ ጊዜ ህልሞች

ብዙዎቹ ህልሞቼ ከመንፈሳዊ ውጊያዎች፥እንዲሁም ከመጨረሻው ዘመን ክስተቶች ጋር የተያያዙ ናቸው።

- በአንደኛው ህልም አብዛኞቹ ትናንሾቹ “ያልበሰሉ ክርስቲያኖች” ተራ በተራ በጠላት እየተዘረፉ እንደሆነ ግልጽ ሆነልኝ። በዛፎች መሀከል ስንሄድ፥ በቡድን፥ ሰይጣንና መልእክተኞቹ እየታገሉ ያሉትን (ደከም ያሉትን) ማጥቃታቸውን ቀጠሉ። ስለዚህም እረኛ ከሆናችሁ፥ መንጎቻችሁን ጠብቁ፥ (በእምነት) ሕፃናቶቹ እንዳይወድቁ ጠብቋቸው።
- በሌላ ህልም፥በከተማ ዙሪያ የደህንነት እርምጃዎች እየጠበቁና እየጠበቁ መጡ፥አንድ ሰው ለመጓጓዝ ብቻ ከተለያዩ ባለስልጣናት ብዙ ፊርማ እስከሚያስፈልገው ድረስ። በዚህም ምክንያት፥ ቀስ በቀስ ራሴን ሕዝብ ከበዛበት ክልሎች ወጣ ወዳሉ ክልሎች አገኘሁት። በሥራ ቦታ ያሉ ጓደኞቼ ‘የአውሬውን ምልክት’ ሊሰጡኝ ሲያሳድዱኝ አየኋቸው። ችግሮቼን ሁሉ ይቀርፍ ይመስል።

---

እባካችሁ፥ ለሕልም ፍቺ ወደ ዓለማዊ ምንጮች አትሂዱ። ፍቺውን ለማግኘት በ**መንፈስ** የተሞሉ ሰዎችን ማግኘት በጣም ከባድ ነው፥እንዲሁም ጠላት ጉዳዩን አስመልክቶ ብዙ ግራ መጋባቶችን ዘርቷል።

በመንፈስ ቅዱስ አብሮን ለሠራ ለአምላካችን ለእስራኤል ቅዱስ የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ምስጋና ይሁን፥አሜን።
ከእንግሊዘኛ ወደ አማርኛ ትርጉም ሙሉነህ አዲሱ
Translated to Amharic by Muluneh Addisu, shalommuluneh@gmail.com